# ምነው ጠፋህብን ብላችሁ ለጠየቃችሁኝ መልስ
# ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ)

ለጥቂት ጊዜ ለምን ከማሕበራዊ መገናኛዎች እንደራቅኩኝ ደብዳቤዎች ደርሰውኛል። እኔ እና ጥቂት ሰዎች በተቻለን ያህል የወያኔዎቹ ፋሺስታዊ ስርዓትም ሆነ በፋሺስቶቹ ጉያ ሆነው ከነገዳዊ ፖለቲካ እምነታቸው ሳይርቁ ነገር ግን እንደ ሁኔታው አመቺነት እየተገላበጡ፤ ለፖቲካ መድረክ ያበቁዋቸው ጌቶቻቸው ወያኔዎችን በመቃዋም ፤ "ውጭም ሆኑ ውስጥ አገር ያሉትን ተቃዋሚዎችን የሚማርክ" ለጀሮ የሚጥም ንግግርም ሆነ አዳዲስ የእምቢተኛነት እርምጃ ሲያራምዱ በማየት የተማረኩ ተቃዋሚዎች "የነገድ ፖለቲካ" "ክፉ በሽታ በደምብ ያልገባቸው ተቃዋሚዎች በሚረጩት ስሜት የጋለበው ትንተና በየመድረኩ ማድመጡና መነታረኩ ስለቀፈፈኝ እስኪበርድላቸው በሚል ርቄ ነበር። ዛሬም እንደዚያው መቀጠሌ አይቀርም።

አንዳንዶቹ በሚገርም ሁኔታ የወያኔን ፋሺስታዊ ስርዓት ሲያራምዱ የቆዩ እና ዛሬም በስርዓቱ ውስጥ ሆነው ስርዓቱን በክልላዊ ፋሺዝም ለማጠናከር የሚጥሩትን የወያኔ መሳሪያዎችን "የሥላሴ ምስጢሮች ናቸው" እየተባሉ የፋሺስት ነገድ ፖለቲካ የሚያራምዱትን እንደ <የኦፒዲኦ> ሰዎች ሁሉ፤ የሚገባውን ማበረታቻ ከመለገስ ይልቅ ከሚገባቸው በላይ አጉልቶ በማጋነን "ከሰማዩ ሰማይ የወረደ ትዕዛዝ ተቀብለው ኢትዮጵያን ለማዳን የተሰለፉ ሙሴያውያን" እያስመሰሉ የሚጽፉ በማየቴ ወደ እውነታው እስኪመለሱ ድረስ አሁንም ትንሽ ለመራቅ ወስኛለሁ።

ይህ በስሜት የመጋለብ ክስተት አዲስ አይደለም። የስየ አብርሃን ፖለቲካ በመጠራጠራችን የደረሰብን ዘለፋ ስናስታውስ፤ አሁን ላላው የኦሮሞዎቹ የቄሮ እና የኦፒዲኦ ሰዎች መላቅጡ ያልለየው እንቅስቃሴ መተቸት የዚያን ያህል ዘለፋ አስከትሎብናል። በየኢመይላችን የሚደርሱንን እያነበብን ነው።ታስታውሱ እንደሆነ "ስየን፤"ኦ ኤል ኤፍ" ሌንጮ ለታን፤ዲማ ነገዎን፤ የኦጋዴን አስገንጣዮችን የሚመራው ሶማሌው የሲያድ ባሬ የበባሕር ሃይል ከፍተኛ ሓላፊ ሆኖ ሲያገልግል የነበረው የዚህ ድርጅት ያሁኑ መሪ ነኝ ባዩ አድሚራል መሀመድ ዑመር ዑስማን ተከታዮች የሆኑት እነ ተወካዮች እነ "አብዱ አብደል ሐኪም" ከግንቦት 7ቱ ከነ ብርሃኑ ነጋና ንአምን ዘለቀ የመሳሰሉትን (አትላንታ ኮነፈረንስን ተመልከቱ 2010 ፈረንጅ አቆጣጠር ) በየ አገሩ እየዞሩ ስለ ጥምረታቸውና አንድነታቸው አብረው ሲያቦኩና ሕዝብን ሲያስጨበጭቡ የነበሩት ዛሬ ያንን ታሪካቸውን ረስተው ስለ ኦጋዴኖች እየተንጫጩ ያሉት እነ ጌታቸው በጋሻው ወዘተ......የመሳሰሉትን ስንቃወምም ሆነ ነጋሶ ጊዳዳን፤ጁነዲን ሰዶን፤ዳዊት ከበደን..." በመጠራጠራችን እና አንዳንዶቹም "የአውራምባው ዳዊት ከበደን" ወያኔ ነው ሲሉን ስንዘልፋቸው እንደነበረው ዐይነት፤ ዛሬም "እነ ቄሮዎችን፤እነ ለማ መገርሳን (የኢትዮጵያ ሙሴ)፤እነ አብይ እነ በቀለ ገርባ....እነ አባ ዱላ (ዛሬ ምላሳቸውን በሐፍረት የቆረጠሙ ሰዎች፤ "አባ ዱላ የመልቀቂያ ደብዳቤ በማስገባቱ "ባንዴ ወንጀሉን ፍቀው' ሰማይ ሰቅለውት እኔን በኢመይል በስድብ የገረፉኝ ሰዎች ነበሩ) የመሳሰሉ "የፖለቲካ ሰዎችና

ስብስቦች' መተቸት አሁን በጋለው የስሜተኞቹ የእሳት ብረት ስለሚያስለበልብ፤ ውዥምብሩን በታዛቢነት ማሳለፍ መርጫለሁ።

ሌላው በተጨማሪም ተቃዋሚ ነን ብለው በተቃዋሚ የቆሙ ትግሬዎች 'በዘመነ ወያኔ' ትግሬዎች ተጠቃሚ አይደሉም" የሚል የከረፋ "ዲፈንስ" (አለማመን ትብሎ) የሚያቀርቡት በተጨባጭ ለምናቀርበው ትንታኔ አንዲትም ሐረግ መልስ ሳይመቱ "በደፈናው" ተጠቃሚ አይደለም የሚለው "ዲፈንሲቭ" ስመለከት ተቃዋሚው እራሱን ለመፈተሽ ነባራዊውን ሁኔታ እስኪጋፈጥ ድረስ እርፍት አስፈልጎኛል።

ይህ ብቻ እንዳይመስላችሁ! እነ ዳዊት፤ጌታቸው በጋሻው እና ወንጀለኛው ድርጅት የመራው ኦነጉ ደ/ር ዲማ ነገዎ በሕብረት ያወጡትን "የአጋዴን ነፃ አውጪ" ከሃዲነትን አስመልክተው ያስጠነቀቁበትን መግለጫ ስመለከት፤ ጌታቸው በጋሻው እራሱ ከብርሃኑ ነጋ ጋር ሆኖ በየአዳራሹ እየዞረ ስለ ኦጋዴኖቹም ሆነ ስለ ኦነጎች ምን ይለን እንደነበር ስለምናስታውስ፤ ይህ ተቃዋሚ ዛሬም ራሱን ሳይፈትሽ በቆሸሸው ሕሊና ሲመጻደቅ መስማት አንዱ ወደ ድረገፆች መምጠቱ ካስጠላኝ ከምክንያቶቹ ተጨማሪ እነዚህና የመሰሉ ናቸው። ስለሆነም ያላነበባችሁኝም ምክንያት ይህ ነው። (EPRDF Version 2 ለማጠናከር የሚሯሯጡትን እነ ሻለቃ ዳዊት፤ ጌታቸው በጋሻው፤ እና እነ ዲማ ነገዎ የሚያቦኩት ስለ ኦጋዴኖቹ የነበራቸው ተስፋና ግንኙነት ሁኔታ በሌላ ርዕስ በሌላ ቀን እመለሳለሁ፤ ያኔው እውነቱን ታያላችሁ።

እስኪ ይህንን እንደ መመረቂያ የሚከተለውን ታሪክ የተወልን እራሳቸው ጣሊያኖች የዘገቡትን የፊልም ማሕደር ተመልከቱና "የሰሞኑ የዓድዋዎቹ ምኒልክን የመዝለፍና የመወንጀል የትምክሕትና የውሸት ትረካ ባዶነት" ለማመዛዘን እንዲረዳቸው ይህንን ጀባ ብየ ልሰናበታችሁ። መችም ምኒልክን ነጻ አውጣን ተብሎ ኡ! ኡ! ድረስልን ተብሎ ነፃ ከተወጣ በኋላ መልሶ ነፃ አውጪውን መወንጀል በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም ከቶ አይታወቅም። ይሕ የትግዎች አስገራሚ ክሕደት ዳዊት ገብረእግዚአብሔር የተባለ ነጋዴ ትግሬ ሚሊዮነር <<ባድሜ የትግሬ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለም! ባድሜ ነጻ የወጣችው በትግሬዎች እንጂ በኢትዮጵያውያን አይደለችም!> የሚለው ሕዝብን ያስደመመ ክሕደት መስማት ትግሬዎች ምንነታችን የተነበበበት ወቅት መሆኑን ስገነዘብ ትግሬነቴን መፋቅ ብችል፤ በፈቀድኩ ነበር።

በሚከተለው የቪዲዮ ማሕደር እና በዶ/ር ተኮላ ወ/ሐጎስ Democratization? Ethiopia (1991-1994) መጽፍ የጻፈውን ልሰናበታችሁ።

ወያኔዎችን እንዲህ ይላቸዋል።
<< There is no doubt in my mind that we are witnessing in Ethiopia the reestablishment of an alternative feudal structure to that of Emperor Haile Selassie, an 'improved and strengthened' royal house, that is regaining political ground lost in the last one hundred class since the overthrow of Emperor Yohannes IV, and more recenmtly as a Specifically, it seemed that the

grandchildren of Sebagadis in consolidating their sprawling relation to start another feudal dynasty in Ethiopia, and to that ened hoodwincked the tens of thousands of freedom fighters, the semi-professional people, to fight and die believing that they were fighting for the liberation of oppressed Tygreans in particular and for the freedom of all Ethiopians in general.

..When I examined the background of other individuals who are placed in the elaboration command structure of the TPLF, I was absolutely flabbergasted to realize that the power structure of the TPLF closely follows and repeats the feudl structure of the Tigreans aristocratic power setup of earlier times with very negligible exceptions. The only novelity this time is the substitution of the old order by their grandsons and sons who spew radical ideologies. This duplication of the past feudal structure in current power structure of the TPLF is so faithfully duplicated that it is absolutely incredible for a fact that the members of the TPLF are not talking about it openly..............> .....Therefore, it is clear that the TPLF forces are led by the sons of feudal warlords camouflaged as liberation front fighters.>> Democratization? Ethiopia (1991-1994)Tecola W.Hagos p11-14)

ወያኔዎች እንዲህ በጥንት ፊውዳለዊ የዙፋን ግንባታ ሥርዓት ተገንብተው "ወያኔ" ሲባሉ፤ እስላሞችም "አህመድ ግራኝን "የነጻነት ታጋይ" በሚል መፈክር ከተሰለቡ፤ እንዲሁም "ኦሮሞዎችም" በቄሮ የሚጠሩት የዛሬዎቹ ኦሮሞ ወጣቶች ደግሞ "ስማቸው" ያገኙት በወታደራዊ ወረራና አመጽ እየተመራ <u>የወንድ ብልትን በመስለብ</u> ባህል ሲያደርግ የነበረው "የገዳ ስርዓት" የተገኘ ነው ስንባል፤ አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ የገዳ ተከታዮች የራሳቸው ዓረባዊ ሰንደቃላማ ተክለው "በዛሬው ዘመን የገዳ ሥርዓት እከተላለሁ" የሚል ማሕበረሰብ፤ ድርጅትና ወጣት፤ ስንመለከት "ፖለቲካ ነውና" የገዳ ስርዓት አወቃቀር እና ተግባር "ቆም" ብለን እንድናስብና እንድንመርምር ያደረግናል እላለሁ።

አሁን ወደ እነዚህ የቪዲዮ ፋይሎች ልውሰዳችሁ። አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ) getachre@aol.com

Tigray (AGAME) Ethiopians WORSHIPING Italian Colonialist in Ethiopia

**https://youtu.be/mXKCyO_Yrp8**

The Mutilated Eritrean Tigray Askaris During Ethiopian Italian War!

**https://youtu.be/_20tOa8C6VU**

Eritrea late 1800 to present ...
**https://youtu.be/-Ii7lo5qEL4**

Eritrea's Last Stand (1941)
**https://youtu.be/blEmpAgn-6I**